# የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) 24ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል በዋሽንግተን ዲሲ ከመቼውም ጊዜ በደመቀ ሁኔታ ተከበረ

በመቶ የሚቆጠሩ በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው የሚኖሩ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች በተገኙበት የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲዊ ድርጅት (ኦህዴድ) 24ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በደማቅ ሁኔታ መጋቢት 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ተከብሯል፡፡



የዕለቱ የምሥረታ በዓል አከባበር የተጀመረው በቅርቡ ከዚህ ኣለም በሞት ለተለዩትና የድርጅቱ መሪ ለነበሩት ለጓድ አለማየሁ አቶምሳና ለትግሉ ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማድረግ ሲሆን፣ በአሜሪካ የኦህዴድ የመሠረታዊ ድርጅት አባል የሆኑት ጓድ ንጉሴ ቢራቱ  የእንኳን አደረሰን ንግግር

አድርገዋል፡፡ በሰሜን አሜሪካ የኦህዴድ ኮሚቴ አመራር አባል የሆኑት ጓድ መላኩ በዳዳ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ያወጣውን ድርጅታዊ መግለጫ አቅርበዋል፡፡



በበዓሉ ላይ ተካፋይ የነበሩ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም በተወካዮቻቸው አማካይነት በየተራ ባሰሙት የድጋፍ ንግግር ኦህዴድ በኦሮሚያ ክልልና በፌዴራል ደረጃ አገራችንን ከድህነት ለማላቀቅና ዴሞክራሲዊ አሰራርን ለማስፋፋት ያደረገውን ተጋድሎ በማድነቅ በመጪዎቹ የትግል ዘመናትም ከጎኑ እንደሚቆሙና አገራችንን ወደ ብልፅግና ምዕራፍ እንደሚያሸጋግሩ አረጋግጠዋል፡፡

በበዓሉ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ግርማ ብሩ **"የኦሮሞ ህዝብ የመብት ጥያቄና የኦህዴድ ትግል መስመር ትክክለኛነት "** በሚል ርዕስ የኦሮሞን ህዝብ የትግል ታሪክና፤ ኦህዴድ አቅጣጫውን በመቀየስ ከሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ጋር በመሆን ከድል ወደ ድል እንዴት ተሸጋግሮ እዚህ ምዕራፍ ላይ እንደደረሰ ገለፃ አቅርበዋል፡፡



አገሪቱን ካለችበት ችግር ለማላቀቅ ድርጅቱንና ህዝቡን ገና ብዙ ትግል እንደሚጠብቃቸው በመጥቀስ ኦህዴድ ይህን ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ጥራት ያለው የትግል መስመር፣ ብቃትና ቁርጠኝነት ያላቸው አባላትና አመራሮች እንዳሉት እንደሚተማመኑ ገልፀዋል፡፡

በፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ በአራቱም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ተወካዮች አማካይነት የሻማ ማብራትና የኬክ ቆረሳ ሥነ-ስርዓት ተከናውኗል፡፡

